# በወልድያ ሰላማዊ የጥምቀት አከባሪዎች ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ ያስቆጣው የወሎ ህዝብ ከወያኔ ጋር ትንቅንቅ ውስጥ ነው (አስናቀው አበበ)

በራያ ቆቦ ከፍተኛ የሆነ ህዝባዊ አመፅ እየተካሄደ ነው። በስርአቱ ንብረትና ተቋማት ላይ ህዝቡ ጥቃት እየወሰደ ነው። ከባድ ተኩስም እንደ ቀጠለ ሲሆን ቁጥሩ ያልታወቀ ሰው ከህዝቡም ከአጋዚም መውደቁ እየተዘገበ ነው።
ወደ ትግራይ የሚያሳልፈው መንገድ በህዝቡ ተዘግቷል።

አሁን አዲስ የመጣው መረጃ ግን አስደንጋጭ ነው። ወያኔ በህዝቡ ላይ ሄሊኮፕተር እንዳዘመተ መረጃ እየወጣ ነው። ይህ እውነት ከሆነ ከቅርብም ከሩቅም ያለ ህዝብ ካልተረባረበ እልቂት ሊያስከትል ነው። ወያኔ የከፈተውን ሁለገብ ጦርነት ለመመከት በአቅራቢያው ያለው የጎጃም፣ የጎንደርና የሸዋ ህዝብ እንዲደርስ ጥሪ እየተላለፈ ነው። ከወልቂጤ እስከወለጋ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመፅም ወሎ ውስጥ ካለው ጋር ተዳምሮ ሃገሪቱ የቀውስ ቀጠና ውስጥ ናት። ህዝቡ ተረባርቦ ወያኔን ካላስወገደ በየተራ ማለቅ ስለሆነ በተቀናጀ መልኩ ትግሉ እንዲቀጥል ጥሪ ሲተላለፍ ከርሟል።
የተቀናጀ የህዝብ ትግል ያሸንፋል





